የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፮ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No 21
ADDIS ABABA, 4th April, 2024


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፭፻፵፬/፳፻፲፮
የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............................ ገጽ ፲፭ሺ፫፻፴፭


## ደንብ ቁጥር ፭፻፵፬/፳፻፲፮

## የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፳፻፲ አንቀጽ ፳፯ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር ፭፻፵፬/፳፻፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩/ "ደን አልሚ" ማለት በይዞታው ላይ ደንን ለተለያዩ ዓላማዎች የሚያለማ፣ የሚጠብቅ እና የሚጠቀም ሰው ነው፣

፪/ "አነስተኛ የግል ደን አልሚ" ማለት በግል ይዞታው ላይ ስፋቱ ከ፭ ሄክታር በታች የሆነ ደንን የሚያለማና የሚጠቀም ሰው ነው፣

## Content


Regulation No 544/2024
Council of Ministers Forest Development, Protection and Utilization Regulation ……………………………………….Page 15335


## REGULATION NO 544/2024

## COUNCIL OF MINISTERS FOREST DEVELOPMENT, PROTECTION AND UTILIZATION REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 27 of the Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation 1065/2018.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1.Short Title

This Regulation may be cited as the "Forest Development, Protection and Utilization Regulation No.544 /2024".

### 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "**Forest Developer**" means a person who develops, protects and utilizes a forest for various purposes on his land holding;

2/ "**Small-Scale Private Forest Developer**" means a person who develops and utilizes a forest of less than 5 hectares on a private land holding;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 448.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፫/ **"ሰፋፊ የግል ደን አልሚ"** ማለት በግል ይዞታው ላይ ስፋቱ ፭ ሄክታርና ከዛ በላይ የሆነ ደንን የሚያለማና የሚጠቀም ሰው ነው፤

፬/ **"የተቋም ደን አልሚ"** ማለት በዕምነት ተቋማት፣ በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ይዞታ ላይ ደንን የሚያለማ፣ የሚጠብቅና የሚጠቀም ሰው ነው፤

፭/ **"የአሳታፊ ደንና የደን መሬት አያያዝ ተጠቃሚ"** ማለት በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኝ ደንና የደን መሬትን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም መብት የተሠጠው የማህበረሰብ አካል ነው፤

፮/ **"የማህበረሰብ ደን አልሚ"** ማለት በአንድ አካባቢ የሚኖር በባህላዊ መንገድ ወይም በህግ በተሰጠው ይዞታ ላይ ወይም ማህበረሰብ ተፋሰስ ውስጥ በሚገኝ መሬት ላይ ደንን በጋራ የሚያለማ፣ የሚጠብቅ እና የሚጠቀም የህብረተሰብ ክፍል ነው፤

፯/ **"የደን ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት በህብረት ስራ ማህበራት ህግ መሠረት ደንን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም እንዲሁም ለደን ልማት የሚሆኑ ግብዓቶችን ለማቅረብ፣ የደን ምርቶችን ዕሴት ለመጨመር ወይም ወደ ገበያ ለማቅረብ የተደራጀ ህጋዊ አካል ነው፤

፰/ **"የማህበራት ደን አልሚ"** ማለት በህብረት ስራ ማህበራት ያልታቀፈ በሌሎች አግባብ ባለቸው ህጎች መሠረት ደንን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም የተደራጁ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ሙያ ማህበራት ወይም በማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ማኅበርን ጨምሮ በሌላ ህግ የተደራጀ ደን አልሚ ነው፤

3/ **"Large-Scale Private Forest Developer"** means a person who develops and utilizes a forest of five hectares or more on private land holding;

4/ **"Institutional Forest Developer"** means a religious institution, government, or non-governmental organization, which develops, protects, and utilizes a forest on its own land holding.

5/ **"Beneficiary of Participatory Forest Land Management"** means the community that has been granted the right to develop, protect and use forest and forest land under government holding;

6/ **"Community Forest Developer"** means a community living in an area, which jointly develops, protects, and utilizes a forest on communal land or on a catchment whose holding has been conferred legally or traditionally.

7/ **"Forest Cooperative"** means a legal entity organized under the Cooperative Societies Legislation to develop, protect and utilize forests, supply inputs, to add value or market forest products;

8/ **"Association Forest Developer"** means a forest developer including youth, women, professional associations or community watershed development association, which is not a member of a forest cooperative, but is organized under the auspices of other appropriate legislations to develop, protect and utilize forests;

CS CamScanner

፱/ "**ኮንሴሽነር**" ማለት በጨረታ ወይም በሌላ መንገድ የመንግሥትን ደን በኮንሴሽን የማልማት፣ የመጠበቅ እና የመጠቀም መብት የተሰጠው ሰው ነው፤

9/ "**Concessionaire**" means a person who has been granted the concession right through auction or other means to develop, protect and utilize state forest.

፲/ "**ለኢኮኖሚ አገልግሎት የለማ ደን**" ማለት ለማገዶ፣ ለግንባታ፣ ለኢንዱስትሪ ወይም ለሌላ ኢኮኖሚያዊ አላማ በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ የለማ ደን ነው፤

10/ "**Forest developed for economic benefits**" means plantation or natural forest developed for construction, industry, fuel wood or other economic benefits;

፲፩/ "**ለአካባቢ ጥበቃ ዓላማ የለማ ደን**" ማለት በዋናነት ለተፋሰስ ልማት፣ የተራቆተ የደን ገጸ-ምድርን፣ ውሃ አዘል መሬቶችን፣ የውሃ ዳርቻዎችን እና የውሃ ማማ አካባቢዎችን ለመጠበቅ የለማ ደን ነው፤

11/ "**Forest developed for Environmental Protection**" means a forest primarily developed for watershed management, protecting degraded forest land, wetlands, riparian areas and water towers;

፲፪/ "**የከተማ ደን**" ማለት በከተማ ውስጥና ዳርቻ ቦታዎች ለተለያዩ ዓላማዎች በሰው ሰራሽ መንገድ የለማ ወይም በተፈጥሮ የበቀለ የዛፎች ወይም የዕጽዋት ክምችት ነው፤

12/ "**Urban Forest**" means a collection of trees or plants that have been planted or grown naturally in urban and suburban areas to provide various services.

፲፫/ "**የደን መመናመን**" ማለት የደኑ አካባባዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ስነ-ህይወታዊ ሀብት ከነበረበት ይዘት ሲቀንስ ነው፤

13/ "**Forest Degradation**" means the reduction of a forest's environmental or economic benefits or biological resources from a better to worse state.

፲፬/ "**የደን ምንጣሮ**" ማለት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ደንን በመመንጠር የደን መሬቱን ወደ ሌላ የመሬት አጠቃቀም መቀየር ነው፤

14/ "**Deforestation**" means changing a forest land to another land use by illegally clearing the forest.

፲፭/ "**ደን መከለል**" ማለት ደኑ ወይም የደኑ መሬት የሚገኝበትን ቦታ በመለየት፣ ቋሚ ምልክት በመትከል ወይም በመሰየም ወይም በማኖር ለደኑ ካርታ ማዘጋጀት ማለት ነው፤

15/ "**Forest Demarcation**" means preparing a forest map by identifying the location of a forest or forest land, and by erecting pillars, naming or putting a permanent sign;

፲፮/ "**የደን ሀብት ቆጠራ**" ማለት የደን ሀብቶችን ጥራትና መጠን በተመለከተ መረጃ መሰብሰብና መመዝገብ ነው፤

16/ "**Forest Resource Inventory**" means collecting and documenting data on the quality and quantity of forest resources.

፲፯/ **"የደን መረጃ ቋት"** ማለት ሀገራዊ የደን ሽፋን፣ የደን ውጤቶች፣ የደን አደጋዎች፣ በደን ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች እና ኢንዱስትሪዎች፣ የደን ውጤቶች ፍላጎትና አቅርቦት፣ዋጋ እና የመሳሰሉትን የያዘ የመረጃ ቋት ነው፤

17/ **"Forest database"** means a source of information on national forest cover, forest products, forest disasters, businesses and industries engaged in the forestry sector, demand and supply of forest products, prices, etc.

፲፰/ **"የደን አደጋዎች"** ማለት በደንና በደን መሬት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የእሳት፣ የበሽታ፣ የተባይ፣ የወራሪ እጽዋት እና የደን መመናመንና መራቆትን የሚያስከትሉ አደጋዎች ነው፤

18/ **"Forest disasters"** means disasters that cause damage to forests and forest land, such as fire, disease, pests, invasive plant species, deforestation, and forest degradation.

፲፱/ **"የኮንሴሽን ውል"** ማለት የመንግስት ደንን ለማልማት፣ ለመጠበቅ ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል በመንግስትና በኮንሴሽነር መካከል የሚደረግ የውል ስምምነት ነው፣

19/ **"Concession contract"** means a contract agreement signed between the government and the concessionaire for the development, protection or utilization of a state forest;

፳/ **"መተዳደሪያ ደንብ"** ማለት የደን አልሚዎች የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ስራዎችን ለማከናወን እንዲያስችላቸው በጋራ ተስማምተው የሚያወጡት ውስጠ ደንብ ነው፣

20/ **"By-laws"** means an internal regulation that forest developers consensually put in place to enable them implement forest development, protection and utilization activities;

፳፩/ **"የሙያ ብቃት ማረጋገጫ"** ማለት በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ ለማማከር፣ ለጥናትና ለምርመር፣ ለስልጠና እና መሰል አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ምስክር ወረቀት ነው፣

21/ **"Certificate of professional competence"** means a certificate, which allows for providing consulting services, research, training and similar services concerning forest development, protection and utilization;

፳፪/ **"ከሰል"** ማለት ዕጽዋትን በከፊል በማቃጠል የሚገኝና እሴት የተጨመረበት የደን ውጤት ነው፣

22/ **"Charcoal"** means a forest product produced by adding value through the carbonization of wood using traditional or modern method;

፳፫/ **"ባለ ቅርፅ ከሰል"** ማለት ከእንጨት ወይም እንጨት ነክ ካልሆኑ የደን ውጤቶች ወይም ከተለያዩ ተረፈ ምርቶች የሚመረት አማራጭ የኃይል ምንጭ ነው፣

23/ **"Briquette"** means a source of alternative energy produced from wood or non-wood forest products or from various plant by-products;

CamScanner

፳፬/ "**የደን ካርበን መጠን**" ማለት በደን ልማትና ጥበቃ የተከማቸ ካርበን ወይም የተቀነሰ የካርበን ልቀት መጠን ነው፤

24/ "**Forest Carbon Stock**" means the amount of carbon sequestered or reduced emissions gained through forest development and protection;

፳፭/ "**የደን ካርበን ምዝገባ**" ማለት በደን ልማትና ጥበቃ የተገኘውን ካርበን ክምችት በሀገራዊ የምዝገባ ቋት መመዝገብ ነው፤

25/ "**Forest Carbon Registration**" means the measurement and registration of carbon stock accumulated as a result of forest development and protection in the national registry database;

፳፮/ "**የደን ካርበን ባለቤትነት መብት**" ማለት በደን ውስጥ ካርበን በማከማቸት ወይም የካርበን ልቀትን በመቀነስ የሚገኝ የካርበን ባለቤትነት መብት ነው፤

26/ "**Forest Carbon Ownership Right**" means ownership right of carbon stock gained through carbon sequestration or reduced carbon emissions;

፳፯/ "**የደን ካርበን ጥቅም ተጋሪነት**" ማለት ከካርበን ግብይት የሚገኘውን ገንዘብ በሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች መካከል የሚደረግ የጥቅም ክፍፍል ነው፤

27/ "**Forest Carbon Benefit Sharing**" means sharing the benefits from carbon trading among eligible beneficiaries;

፳፰/ "**የደን ሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ**" ማለት በደን መኖር ምክንያት የሚገኙ የመጠጥና የመስኖ ውሃ እና የሀይል አቅርቦት፣ ከጎርፍና ከደለል አደጋ መጠበቅ እና የመሳሰሉት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ለደን አልሚው የሚከፍሉት ክፍያ ነው፤

28/ "**Payment For Forest Ecosystem Services**" means payment made to the forest developer by beneficiaries of ecosystem services for the provision of drinking and irrigation water, the supply of electric energy, and for protection from flood

፳፱/ "**ሚኒስቴር**" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

29/ "**Ministry**" means the Ministry of Agriculture;

፴/ "**የኢትዮጵያ ደን ልማት**" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተቋቋመ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ነው፤

30/ "**Ethiopian Forest Development**" means the executive body of the federal government established in accordance with Article 48 Sub-article 1 of Proclamation No. 1263/2021;

፴፩/ "**አዋጅ**" ማለት የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ ነው፤

31/ "**Proclamation**" means Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation 1065/2018;

## ክፍል ሁለት

## ስለ ግል ደን

### ፫. የግል ደን ባለቤቶች

የግል ደን ባለቤቶች የሚከተሉት ናቸው

፩/ አነስተኛ ደን አልሚ

፪/ ሰፋፊ ደን አልሚ

### ፬. የአነስተኛ የግል ደን አልሚ መብቶች

የአነስተኛ የግል ደን አልሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል ፡-

፩/ የኤክስቴንሽን፣ የስልጠና እና ሌሎች የሙያ ድጋፎችን የማግኘት፣

፪/ ደኑን ሲያለማ፣ ሲንከባከብና ሲጠቀም በዘላቂ መንገድ ስለማስተዳደሩ የምስክር ወረቀት የማግኘት፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፣

፫/ ባለማው ደን ውስጥ የሚገኝ የደን ካርበን ባለቤት የመሆን፣

፬/ ካርበንን ጨምሮ የደን ምርቱን ባለቤትነት መብት ለሌላ ወገን የማስተላለፍ፣

፭/ ከሚያለማው እና በይዞታው ስር ከሚገኝ ደን የካርቦን ሽያጭና ሌሎች ስርዓተ- ምህዳራዊ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ የመሆን፣

፮/ የደን ካርበን ባለቤትነት መብቱን ሲያስተላልፍ የመንግስት የአስተዳደርና የሙያ ድጋፍ የማግኘት፣

፯/ ያለማውን ደን ወይም የደኑን መሬት በዋስትናነት በማስያዝ የብድር እና የመድህን ዋስትና አገልግሎት የማግኘት፣

፰/ በመጥፋት ላይ ያሉ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ሲያለማ ማበረታቻ የማግኘት መብት አለው፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## PART TWO

## PRIVATE FOREST

### 3. Private Forest Owners

The following shall be private forest owners:

1/ Small-scale Forest Developer

2/ Large-scale Forest Developer

### 4. Rights of Small-Scale Private Forest Developer

Small-scale private forest developer shall have the following rights:-

1/ Access to extension, training and other professional support;

2/ Award of certificate for developing, tending, utilizing and sustainably managing a forest; details shall be determined by a directive;

3/ To own forest carbon in the forest he has developed.

4/ To transfer ownership right of forest products including carbon to another party.

5/ To receive benefit from the sale of carbon and other ecosystem services generated from the forest developed on the land he holds;

6/ To receive administration and technical support from the government when transferring the carbon ownership right;

7/ Access to loan and insurance by using the forest he developed or the forest land he holds as collateral

8/ The right to receive incentives for planting and developing endangered indigenous tree species; details shall be determined by a directive.

CamScanner

**፭. <u>የአነስተኛ የግል ደን አልሚ ግዴታዎች</u>**

የአነስተኛ የግል ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል ፡-

፩/ በመጥፋት ላይ ያሉ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ሲጠቀም በግል ይዞታው ላይ የለሙ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ የማቅረብ፣

፪/ የተቋም ደን አልሚ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን እና ጥብቅ ደኖችን የማልማትና ጠብቆ የማቆየት፣

፫/ በካርበን ሽያጭ ሂደት ውስጥ የመንግስትን ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ ከካርበን ሽያጭ ገቢው ለፌደራል መንግሰት ፭ ከመቶ እና ለክልል መንግስት ፲፭ ከመቶ የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል፣

፬/ አግባብ ላለው ባለስልጣን ወይም አግባብ ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ለተሰጠው አካል መረጃ የመስጠት እና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፮. <u>የሰፋፊ የግል ደን አልሚ መብቶች</u>**

በዚህ ደንብ አንቅጽ ፬ የተጠቀሱት የአነስተኛ ደን አልሚ መብቶች ለሰፋፊ ደን አልሚም ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

**፯. <u>የሰፋፊ የግል ደን አልሚ ግዴታዎች</u>**

የሰፊ የግል ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

**5. <u>Obligations of Small-Scale Private Forest Developer</u>**

Small-scale private forest developer shall have the following obligations:-

1/ To submit evidence from the relevant body when utilizing endangered indigenous tree species grown on the land he holds;

2/ An institutional forest developer shall develop and sustain the protection of indigenous tree species and protected forests;

3/ To pay a service fee of 5 percent to the federal government and 15 percent to the regional government from revenue generated from the sale of carbon when he needs government support in the process of selling carbon;

4/ To provide information to and cooperate with authorized organization or an entity which is granted permission from the appropriate authority.

**6. <u>Rights of Large-Scale Private Forest Developer</u>**

The rights of small-scale forest developers provided in Article 4 of this Regulation shall also apply to a large-scale forest developer;

**7. <u>Obligations of large-scale private forest developer</u>**

Large-scale private forest developer shall have the following obligations:-

CamScanner

፩/ ደን ለማልማትና ለመጠቀም ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ግምገማና የአዋጭነት ጥናት ሰነድ የማቅረብ፣

፪/ በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሰረት ደኑን የማስተዳደር፣

፫/ በመጥፋት ላይ ያሉ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ከማምረቱ በፊት በግል ይዞታው ላይ የለሙ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ የማቅረብ፣

፬/ በካርበን ሽያጭ ሂደት ውስጥ የመንግስትን ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ ከካርበን ሽያጭ ገቢው ለፌደራል መንግስት ፭ ከመቶ እና ለክልል መንግስት ፲፭ ከመቶ የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል፣

፭/ ደኑን አደጋ ላይ የሚጥል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ባጋጠመው ጊዜ በቅርብ ለሚገኘው የደኑን ዘርፍ ለመምራት ስልጣን ለተሰጠው የመንግስት አካል በወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ፣

፮/ የተቋም ደን አልሚ ከሆነ ሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን እና ጥብቅ ደኖችን የማልማትና ጠብቆ የማቆየት፣

፯/ አግባብ ላለው ባለስልጣን ወይም አግባብ ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ለተሰጠው አካል መረጃ የመስጠት እና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ ማህበረሰብ ደን

### ፰. የማህበረሰብ ደን አልሚ መብቶች

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከቱት መብቶች ለማህበረሰብ ደን አልሚም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

1/ To submit feasibility study and environmental and social impact assessment document prior to developing and utilizing a forest;

2/ To manage a forest according to an approved forest management plan;

3/ To submit evidence from the appropriate authority prior to harvesting threatened indigenous trees grown from a forest he developed on his land holding;

4/ To pay a service fee of 5 percent to the federal government and 15 percent to the regional government from revenue generated from the sale of carbon when he needs government support in the process of selling carbon;

5/ To timely report to the appropriate government body authorized to manage the forest sector when he faces an overwhelming problem, which is beyond his capacity, that threatens his forest,

6/ An institutional forest developer shall develop and sustain the protection of indigenous tree species and protected forests;

7/ To provide information to and cooperate with authorized organization or an entity which is granted permission from the appropriate authority.

## PART THREE
## COMMUNITY FOREST

### 8. Rights of Community Forest Developers

The rights indicated in Article 4 of this Regulation shall apply to the community forest developer.

**፱. <u>የማህበረሰብ ደን አልሚ ግዴታዎች</u>**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱት ግዴታዎች ለማህበረሰብ ደን አልሚ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ስለ ማህበራት ደን</u>**

**፲. <u>የማህበራት ደን አልሚ መብቶች</u>**

በዚህ ደንብ አንቅጽ ፬ የተጠቀሱት የአነስተኛ ደን አልሚ መብቶች ለማህበር ደን አልሚም ተፈጻሚ ይሆናሉ

**፲፩. <u>የማህበራት ደን አልሚ ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የማህበር ደን አልሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ የደኑ ስፋት ከ ፭ ሄክታር በታች ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመላከቱት ግዴታዎች በማህበራት ደን አልሚ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

፪/ የደኑ ስፋት ፭ ሄክታር እና ከዛ በላይ ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተመላከቱት ግዴታዎች በማህበራት ደን አልሚ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

፫/ ያመረተውን የደን ምርት ከቦታ ቦታ ሲያዛውውር ከሚመለከተው አካል የይለፍ ወረቀት የመያዝ፣

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ካላከበረ ለደን ልማት የተሰጠውን መሬት የመጠቀም መብት ያጣል፡፡

፭/ አግባብ ላለው ባለስልጣን ወይም አግባብ ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ለተሰጠው አካል መረጃ የመስጠት እና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**9. <u>Obligations of Community Forest Developers.</u>**

The obligations specified in Article 5 of this regulation shall also apply to the community forest developer.

**<u>PART FOUR</u>**

**<u>ASSOCIATION FOREST</u>**

**10. <u>Rights of Community Forest Developer</u>**

The rights indicated in Article 4 of this regulation shall apply to the Association forest developer.

**11. <u>Obligations of Association Forest Developer</u>**

Association forest developer shall have the following obligations:-

1/ The obligations specified under Article 5 of this Regulation shall also apply to the association forest developer if the area of the forest is less than five hectares;

2/ The obligations specified under Article 7 of this Regulation shall also apply to association forest developer if the area of the forest is 5 hectares or more;

3/ To acquire a permit from the appropriate body for transporting forest products from one locality to another;

4/ If the association forest developer does not comply with the obligations specified in Sub-Article 1 and 2 of this Article, he will forfeit the right to use the land he holds;

5/ To provide information to and cooperate with authorized organization or an entity which is granted permission from the appropriate authority.

CamScanner

## ክፍል አምስት
## ስለ ደን አልሚ ማበረታቻ

### ፲፪. የደን አልሚዎች የማበረታቻ መስፈርቶች

፩/ የግል ደን አልሚዎች ከሊዝ ክፍያ ነጻ የደን መሬት ለማግኘት፣

ሀ) ለወጣቶችና ለሴቶች የተሻለ የሥራ ዕድል የሚፈጥር፣

ለ) ከውጭ የሚገቡ የደን ምርት ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ደን የሚያለማ፣

ሐ) ካርበንን ጨምሮ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የሚችሉ የደን ምርቶችን የሚያመርት፣

መ) የተሻሻሉ የደን ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም፣

ሠ) የማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው ተጨማሪ ዕቅድ ያለው፣

ረ) የተራቆቱ የደን ገጸ-ምድር እና ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን የሚያለማ ደን አልሚ ቅድሚያ ያገኛል፡፡

፪/ የግብር እፎይታ ለማግኘት፣

ሀ) ለአነስተኛ እና የማህበረሰብ ደን አልሚዎች የመሬት ይዞታ ደብተር ማቅረብ፣

ለ) ለሰፋፊ ደን አልሚዎች የመሬት ይዞታ ደብተር፣ የጸደቀ የደን አያያዝ እቅድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ፣

ሐ) ለሰፋፊ ደን አልሚዎች ደኑን በባለቤትነት ከሚያስተዳድረው የደን መስሪያ ቤት በጸደቀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሰረት ለማልሙ እና ለመጠበቁ የጽሁፍ ማረጋገጫ ማቅረብ

## PART FIVE
## INCENTIVES FOR FOREST DEVELOPERS

### 12. Criteria To Incentivize Forest Developers

1/ To access forest land free of lease payment the private forest developer shall;

a) Create job opportunities for youth and women;

b) Develop forest to substitute imported forest products with locally produced products;

c) Produce forest products, including carbon, to generate foreign currency;

d) Use improved forestry technologies;

e) Plan to fulfill its corporate social responsibility;

f) Be given priority if he commits to develop degraded landscapes and areas vulnerable to disasters.

2/ To be granted tax relief;

a) Small-scale and community forest developers shall submit certificate of land holding;

b) Large-scale forest developers shall submit land holding certificate, approved forest management plan, feasibility study, and social and environmental impact assessment document.

c) Submit written evidence from the concerned government authority confirming he has appropriately developed and protected forests based on the approved forest management plan.

፫/ ከአበዳሪ ተቋማት ብድር ለማግኘት

ሀ) ለአነስተኛ እና የማህበረሰብ ደን አልሚዎች የመሬት ይዞታ ደብተር ማቅረብ፣

ለ) ለሰፋፊ ደን አልሚዎች የመሬት ይዞታ ደብተር፣ የጸደቀ የደን አያያዝ እቅድ፣የአዋጭነት ጥናት እና ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ To access loan from lending institutions

a) Small-scale and community forest developers shall submit certificate of land holding;

b) Large-scale forest developers shall submit land holding certificate, approved forest management plan, feasibility study, and social and environmental impact assessment document.

## ክፍል ስድስት
## የመንግስት ደን

### ፲፫. ደንና የደን መሬት መከለልና መሰየም

፩/ ደን እና የደን መሬት የሚከለለው እና የሚሰየመው አግባብነት ካላቸው ተቋማትና በደኑ ዙሪያ ከሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመወያየት እና በመስማማት ይሆናል፤

፪/ የሚከለሉ ደኖች እና የደን መሬቶች በካርታ ላይ ይሰፍራሉ፤ በይዞታው ማረጋገጫ ደብተር መሠረት ድንበርና ቋሚ ምልክትም ይኖራቸዋል፤

፫/ የሀገሪቱ የደን ሀብት ተለይተው ተመዝግበው የሚያዙበት የደን ይዞታዎችን መረጃ የሚያሳይ የመረጃ ቋት ይደራጃል፤

፬/ ደኖች እንደዋና ግልጋሎታቸው ምርት ሰጪ፣ ጥብቅ፣ ወይም ፍጹም ጥብቅ ደን ተብለው ይሰየማሉ፤ ስያሜአቸው እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል፤ አፈጻጸሙ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤

፭/ አንድ ደን የምርት ሰጪ ደን ተብሎ የሚሰየመው የሚከተሉትን መስፈርቶች ሲያሟላ ነው፤

## PART SIX
## STATE FOREST

### 13. Demarcation and Designation of Forest and Forest Land

1/ Forest and forest land shall be demarcated and designated through discussions and agreement reached with appropriate institutions and communities living around the forest.

2/ Demarcated forests and forest lands shall be mapped and shall have boundaries and permanent marks/pillars/signs based on the land holding certificate;

3/ A database shall be organized to identify and register the country's forest resources and to provide information on forest holdings;

4/ Forests shall be designated as productive, protective, or preserved forest based on their primary service; their designation may be changed as required; its implementation shall be determined by a directive.

5/ A forest shall be designated a productive forest when it meets the following criteria:

CamScanner

ሀ) ተርቀህን ጨምሮ በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ የበቀለና የለማ ሆኖ በዋናነት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያለው ሲሆን፣

ለ) ደኑ ምርት ሰጭ ተብሎ በመሰየሙ ምክንያት በስርዓተ-ምህዳርና ብዝሃ-ህይወት ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል ሲሆን ነው፡፡

፮/ አንድ ደን ጥብቅ ደን ተብሎ የሚሰየመው፣

ሀ) ደኑ ብዝሃ-ሕይወትን በውስጡ ለማስጠለል፣ ለመጠበቅ፣ ለማራባት እና ለመንከከብ ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን፣

ለ) የመሬት አጠቃቀሙ ከደን ወደ ሌላ መሬት አጠቃቀም ቢቀየር በስርዓተ-ምህዳሩ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር ሲሆን፣

ሐ) አካባቢው ለመሬት መንሸራተት፣ ለጎርፍ እና ለመሳሰሉት አደጋዎች ተጋላጭ ሲሆን፣

መ) በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ዘዴ እያገገመ ወይም ራሱን እየተካ ያለ ሲሆን፣

ሠ) ለውሀ ማማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ገጸ-ምድር ሲሆን፣

ረ/ ለኢኮቱሪዝም ከፍተኛ አገልግሎት መስጠት የሚችል ሲሆን ነው፡፡

፯/ አንድ ደን ፍጹም ጥብቅ ደን ተብሎ የሚሰየመው፣

ሀ) የደኑ ሥርዓተ-ምህዳር ከፍተኛ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣

ለ) ደኑ በውስጡ ከፍተኛ ሥርዓተ-ምህዳራዊ፣ ትምህርታዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣

a) If it is planted, developed or naturally occurring forest including bamboo, which primarily provides economic benefits.

b) If it does not cause significant negative impact on ecosystems and biodiversity because of its designation as productive forest.

6/ A forest is designated as protected forest;

a) If the forest serves as a center for hosting, protecting, breeding and conserving biodiversity.

b) If the land use changes from forest to other land uses will have a significant negative impact on the ecosystem.

c) If the area is susceptible to landslides, floods, etc.

d) If it is being restored or is regenerating through manmade or natural means;

e) If the landscape serves as a water tower;

f) If it provides a significant contribution to ecotourism

7/ A forest is designated as preserved forest;

a) If the forest ecosystem has significant national, continental, and global importance.

b) If the forest has significant ecological, educational, scientific, historical, and cultural benefits.

ሐ) ደኑ ከፍተኛ የዕጽዋት እና የእንስሳት አይነት፣ ስብጥርና ክምችት ያለው ሆኖ ለተለያዩ ከፍተኛ አደጋዎች ተገላጭ ሲሆን፣

መ) አካባቢው ለከፍተኛ መሬት መንሸራተት፣ ጎርፍ እና ለመሳሰሉት አደጋዎች ተጋላጭ ሲሆን፣

ሠ) እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ መስፈርቶች በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ጸድቆ በሚወጣ መመመሪያ ይወሰናል

## ፲፬. የምርት ሰጭ ደን አጠቃቀም እና አያያዝ

ደኑን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፦

፩/ እንደአስፈላጊነቱ የካርበን ግብይትን እና ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደርገ የደን አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ጥቅም ላይ የሚውለውም በጸደቀው የደን አያያዝ ዕቅድ ይሆናል፣

፪/ በይዞታው ላይ በራሱ ወይም በሽርክና ወይም ሌሎች ህጋዊ አሰራሮችን በመጠቀም ከግል ባለሀብቶችና ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ አዳዲስ የምርት ሰጪ ደኖች ያለማል፣

፫/ ለምርት የደረሱ ደኖች ሲሸጡ ደኑ ለሚገኝበት ቀበሌ ማህበረሰብ ለጋራ አገልግሎት ሊውል የሚችል ከሽያጭ ፲ ከመቶ ለቀበሌው ማህበረሰብ ይከፍላል፤

c) If the forest has important plant and animal types, diversity, and stock which are vulnerable to various disasters.

d) If the area is vulnerable to landslides, floods and similar disasters;

e) As necessary, additional criteria will be determined by a directive approved by the Ministry

## 14. Use and Management of Productive Forest

The organization authorized by law to manage the forest shall:

1/ Prepare a forest management plan that considers trading and benefitting from carbon as appropriate; the forest shall be utilized in accordance with the approved forest management plan.

2/ Develop new production forests on its land holding on his own or through joint venture or other legal means by collaborating with private business owners and communities to supply forest industries;

3/ Pay 10 Percent of the revenue from the sale of forest products to the local community where the forest is located where upon the money shall be used for the provision of shared community services;

፬/ በይዞታው ያለውን የምርት ሰጪ ደን የማልማት፣ የመጠበቅ፣ የመጠቀም እና የማስተዳደር መብትና ኃላፊነቱን ለማህበረሰብ፣ ለማህበራት ወይም ለግል ደን አልሚዎች በኮንሴሽን ወይም በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት መሠረት በውል ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ውሉም የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፣ ውሉ የሚቋረጥበትንና ይግባኝ የሚጠየቅበትን አሰራር ያካተተ ሆኖ ደኑን ለኮንሴሽነሩ ለማስተላለፍ ስልጣን የተሰጠው አካል በሚገኝበት አስተዳደር እርከን ባለ የፍትህ አካላት መጽደቅ ይኖርበታል፤

፭/ ለምርት ሰጪ ደን አገልግሎት ሊውል የሚችል የደን መሬትን በመለየት በአሳታፊ ደን አያያዝ ሥርዓት፣ በተደራጁ የደን አልሚዎች ወይም በግል ባለሃብቶች እንዲለማ፣ እንዲጠበቅ እና ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፮/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት በአሳታፊ ደን አስተዳደር ስር ካሉ የምርት ሰጪ ደኖች ቀርከሃንና ከሰልን ጨምሮ እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

፯/ ከካርበን ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎች እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፭. <u>የጥብቅ ደን አስተዳደርና አጠቃቀም ደኑን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል፡-</u>

፩/ የጥብቅ ደኖች በውስጣቸው እንደያዙት ብዝሃ-ሕይወት እና እንደሚገኙበት ሥርዓተ- ምህዳር መሠረት የሚጠበቁበትና ጥቅም ላይ የሚውሉበት የደን አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

4/ Transfer the rights and responsibilities of developing, protecting, utilizing and managing a productive forest in his possession to communities, associations or private forest developers under a concession or participatory forest management arrangement; the contract shall include the rights and obligations of the parties, the procedures for terminating the contract and appeals, and must be approved by appropriate justice organ at the administrative level where the party authorized to transfer the forest to the concessionaire is located;

5/ Identify forest land for production forest that could be developed, protected and utilized through participatory forest management, by organized forest developers or by private investors;

6/ Sell the wood-based forest products, including bamboo and charcoal, from productive forests by involving the community based on the forest management plan;

7/ Ensure that the revenue from carbon sales is used for forest development, protection, and utilization.

15. <u>**Management and Utilization of Protected Forest**</u>

The organization authorized by law to manage the forest shall:

1/ Develop a management plan to protect and utilize the protected forest by considering the biodiversity and ecosystem in which they occur;

፪/ የቆላ አካባቢ ደኖች አጠቃቀም እና አስተዳደር የአካባቢውን ህብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ እና ስርዓተ-ምህዳር ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በሚዘጋጅ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ያስተዳድራል፤

፫/ በደን ውስጥ ለጥቅም መዋል የሚገባቸው የደን ውጤቶች ወይም ግልጋሎቶች ሲኖሩ በደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፬/ የሀገር በቀል ዝርያዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ስብጥራቸው እና ክምችታቸው ግምት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤

፭/ ጥብቅ ደን ላይ ያለውን መብትና ኃላፊነት እንደአስፈላጊነቱ ለማህበረሰብ፣ ለማህበራት ወይም ለግል ደን አልሚዎች በኮንሴሽን ወይም በአሳታፊ ደን አያያዝ ስርዓት መሠረት ሊያስተላለፍ ይችላል፤ ውሉም የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፣ ውሉ የሚቋረጥበትንና ይግባኝ የሚጠየቅበትን አሰራር ያካተተ ሆኖ ደኑን ለኮንሴሽነሩ ለማስተላለፍ ስልጣን የተሰጠው አካል በሚገኝበት አስተዳደር እርከን ባለ የፍትህ አካላት መጽደቅ ይኖርበታል፤

፮/ በተለያዩ ምክንያቶች በጥብቅ ደን ውስጥና ዙርያው የተመነጠሩ ወይም የተመናመኑ የደን ቦታዎችን ሥርዓተ-ምህዳርን ባገናዘበ መልኩ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ መንገድ እንዲለሙ ያደርጋል፤

፯/ ጥብቅ ደኖች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ መጤ እና ወራሪ የዕጽዋት ዝርያዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

2/ Administer the management of forests in lowland dry land areas in accordance with a management plan, which considers the livelihood of local communities and status of the ecosystem;

3/ Ensure that forest products and services are utilized based on a management plan;

4/ Ensure that the utilization of indigenous species considers, their diversity and abundance;

5/ Transfer the rights and responsibilities of the protected forest to communities, associations, or private forest developers, as appropriate, under a concession or participatory forest management arrangement; the contract shall include the rights and obligations of the parties, the procedures for terminating the contract and appeals, and must be approved by the appropriate justice organ at the administrative level where the party authorized to transfer the forest to the concessionaire is located.

6/ Develop deforested and degraded forest lands within and around a protected forest through manmade or natural means, by considering the status of the ecosystem;

7/ Put in place a system for controlling alien and invasive plant species that are harmful to protected forests;

፰/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት በአሳታፊ ደን አያያዝ ስር ካሉ የጥብቅ ደኖች ቀርቀሃንና ከሰልን ጨምሮ እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

፱/ በጸደቀ የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ለጥቅም የደረሱ ቀርቀሃንጨምሮ ዛፎችን ለምርት ዓላማ በጨረታ ሊሸጥ ይችላል፤

፲/ ከደኑ ውስጥ ቀርቀሃን ጨምሮ ዛፎችን ለምርምር ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መፍቀድ ይችላል፤

፲፩/ ከደኑ ውስጥ ምርት ለማምረት በሚያስፈልግበት ጊዜ የአካባቢና የማህብረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፲፪/ ከካርበን ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እንዲያውል ያደርጋል፡፡

፲፮. <u>የፍጹም ጥብቅ ደን አስተዳደርና አጠቃቀም</u>

ደኑን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ፡-

፩/ ፍጹም ጥብቅ ደኖች በውስጣቸው እንደያዙት ብዝሃ-ሕይወት እና እንደሚገኙበት ሥርዓተ-ምህዳር መሠረት የሚጠበቁበትና ለትምህርትና ለምርምር አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉበት እንዲሁም ከማንኛውም ውድመትና ጥፋት ለማዳን የሚወሰዱ ተግባራትን ያካተተ የደን አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

፪/ ከፍጹም ጥብቅ ደኖች ካርበን ሽያጭ ጨምሮ በማናቸውም መልኩ የሚገኝ ገቢ በአሳታፊ የደን አስተዳደር የታቀፉ የአካባቢ ህብረተሰብ ክፍሎች ፹ ከመቶ ፣ ለፌደራል መንግስት ፭ ከመቶ እና ለክልል መንግስት ፲፭ ከመቶ ድርሻ ይኖራቸዋል፤

8/ Sell wood-based forest products, including bamboo and charcoal, from forests under participatory forest management by involving the community based on the forest management plan;

9/ Sell merchantable trees including bamboo for production purpose through auction based on an approved management plan;

10/ May allow the use of trees including bamboo within a forest, for the purpose of research;

11/ Ensure that environmental and social impact assessment document is submitted when it is found necessary to harvest forest products from a protected forest;

12/ Ensure that the revenue from the sale of carbon is used for forest development, protection, and utilization.

16. <u>Management And Use of Preserved Forest</u>

The organization authorized by law to manage the forest shall:

1/ Develop a management plan based on the existing biodiversity within forests and the ecosystem in which they occur for protection, education, and research as well as for preventing damage and destruction;

2/ The federal government, regional government, communities involved in participatory forest management shall share 5%, 15% and 80% of the revenue, respectively from the sale of carbon and other sources of income;

፫/ ከካርበን ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እንዲያውል ያደርጋል፡፡

፲፯. <u>የአሳታፊ ደንና የደን መሬት አያያዝ ተጠቃሚ ያላቸው መብቶች</u>

፩/ ከሚመለከተው አካል የሙያ፣ ስልጠና፣ የህግ እና አስተዳደራዊ ድጋፍ የማግኘት፣

፪/ ደኑን ከሚያስተዳድረው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የደን አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

፫/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ለገበያና ለፍጆታ በነጻ የመጠቀም፣

፬/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ዕጣን እና ሙጫ ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፺ ከመቶ የመጠቀም፣

፭/ በጥብቅ ደኖች ቀርቀሃንና ከሰልን ጨምሮ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፸ በመቶ የመጠቀም፣

፮/ የተራቆቱ የደን መሬቶችን መልሶ ለማልማት በሰው ሰራሽ መንገድ ከለማ ደን በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፺ ከመቶ የመጠቀም፣

፯/ በዘርፉ በተሰማሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሳትፎ በአዲስ መልክ በሰው ሰራሽ መንገድ ከለሙ የመንግስት ደን በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፷ ከመቶ የመጠቀም፣

3/ Ensure that the revenue from the sale of carbon is used for forest development, protection, and utilization.

17. <u>Rights of Beneficiaries of Participatory Forest Management</u>

1/ Receive technical advice, training, legal and administrative support from the concerned party;

2/ Prepare a forest management plan in collaboration with the relevant government body;

3/ Access to non-timber forest products free of charge, for marketing and consumption purpose based on the forest management plan;

4/ Use 90 percent of the income from the sale of incense and gum based on the forest management plan,

5/ Use 70 percent of the income from the sale of wood-based forest products, including bamboo and charcoal, produced within protected forests based on the forest management plan;

6/ Use 90 percent of the income from the sale of wood-based forest products based on the forest management plan prepared for developing plantation forest to restore degraded lands;

7/ Use 60 percent of the revenue from the sale of wood-based forest products produced from state forests based on the management plan which is developed through the participation of government enterprises engaged in the forest sector;

CS CamScanner

፰/ በነባር ሰው ሰራሽ የመንግስት ደን በተዘጋጀው የደን አስተዳደር ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፲ ከመቶ የመጠቀም፣

፱/ ከካርበን ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ ፹ ከመቶ የመጠቀም፣

፲/ ካርበንን ጨምሮ የደን ምርቱን ባለቤትነት መብት ለሌላ ወገን የማስተላለፍ፣

፲፩/ ማህበረሰቡ ካርበንን ጨምሮ ከደኑ የሚያገኘውን ድርሻ በዘርፉ ከተሰማሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣የግል ድርጅቶች ወይም ባለሀብቶች ጋር ህጋዊ ዉል በመዉሰድ ተቀናጅቶ የማልማት፣ የመሸጥና ጥቅም የመጋራት፣

፲፪/ በአሳታፊ የደን አያያዝ ስርዓት ስር የሚተዳደር ደን ለሌላ የተሻለ ሀገራዊ እና ክልላዊ ጥቅም ለሚያስገኝ አማራጭ የመሬት አጠቃቀም የሚወል ከሆነ አስፈላጊውን ካሳ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፰. <u>የአሳታፊ ደንና የደን መሬት አያያዝ ተጠቃሚ ያለባቸው ግዴታዎች</u>

፩/ ለሚያስተዳድሩት ደን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የደን አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በተዘጋጀው ዕቅድ እና የውል ስምምነት መሠረት ተለይተው የተቀመጡትን ተግባራት ማከናወን፣ መከታተል፣ መገምገምና ሪፖርት ማድረግ፣

8/ Use 10 percent of the revenue from the sale of wood-based forest products produced from existing state forest plantations based on the management plan;

9/ Use 80 percent of the revenue from the sale of carbon;

10/ Transfer the ownership right of forest products including carbon to another party;

11/ Jointly develop, sell and share benefits gained from the forest including carbon sequestered in collaboration with non-governmental organizations, private organizations or investors engaged in the forest sector based on a legally binding agreement;

12/ The right to receive appropriate compensation if a forest managed under a participatory forest management system is to be converted to an alternate land use, which will provide greater national and regional benefits; details shall be determined by a directive;

## 18. <u>Obligations of Beneficiaries of Participatory Forest Management</u>

1/ Prepare a forest management plan in collaboration with the relevant government body for the forest they manage; carry out, monitor and evaluate activities outlined in the management plan and the agreement, and submit a report;

፪/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት ዕጣን እና ሙጫ ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፲ ከመቶ ለመንግስት የመክፈል፣

፫/ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት በጥብቅ ደኖች ቀርቀሃን ጨምሮ እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፴ ከመቶ ለመንግስት የመክፈል፣

፬/ የተራቆቱ የደን መሬቶችን መልሶ ለማልማት በሰው ሰራሽ መንገድ ከለማ ደን በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፲ ከመቶ ለመንግስት የመክፈል፣

፭/ በመንግስት የልማት ድርጅት በሚተዳደር የደን መሬት በአዲስ መልክ የሰው ሰራሽ ደን ካለሙ በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፵ ከመቶ ለመንግስት ልማት ድርጅት የመክፈል፣

፮/ በነባር ሰው ሰራሽ የመንግስት ደን በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት እንጨት ነክ የሆነ የደን ውጤት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ፺ ከመቶ ለመንግስት የመክፈል፣

፯/ ከካርበን ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ ፲፭ ከመቶ ለክልል መንግስት፣ ፭ ከመቶ ለፌደራል መንግስት የመክፍል፣

፰/ ከህብረተሰቡ አቅም በላይ የሆነ ችግር ባጋጠማቸው ወቅት በቅርብ ለሚገኘው የደን መስሪያ ቤት በወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ፣

2/ Shall pay 10 percent of the revenue to the government from the sale of incense and gum based on the forest management plan.

3/ Shall pay 30 percent of the revenue to the government from the sale of wood-based forest products including bamboo from protected forests, based on the forest management plan;

4/ Shall pay 10 percent of the revenue to the government from the sale of wood-based forest products based on the forest management plan from forests developed to rehabilitate degraded lands;

5/ Shall pay 40 percent of the revenue to the government from the sale of wood-based forest products produced based on the forest management plan if they develop new plantation on the forest land under the holdings of government enterprises;

6/ Shall pay 90 percent of the revenue from the sale of wood-based forest products produced based on the management plan from existing state forest plantations;

7/ Shall pay 15 percent of the revenue from the sale of carbon to the regional government and 5 percent to the federal government;

8/ Timely report to the nearest forest office when encountering a problem which is beyond the community's capacity;

CamScanner

፱/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፰ የተጠቀሱትንና በውል ውስጥ የተካተቱ ግዴታዎችን በሙሉ ወይም በከፊል ካላከበሩ ከመንግስት ጋር የገቡት ውል ይቋረጣል፡፡

**፲፱. <u>ለደን ኮንሴሽን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፣ የጨረታ ሂደት እና የውሳኔ አሰጣጥ</u>**

፩/ አንድ ደን በኮንሴሽን ውል ለሌላ ወገን የሚተላለፈው ፡-

ሀ) በምርት ሰጪ ወይም በጥብቅ ደንነት የተከለለ፣ የተሰየመ እና ሙሉ መረጃ ያለው፣

ለ) የደን አያያዝ ዕቅድ የተዘጋጀለት፣

ሐ).የአካባቢና ማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ የተዘጋጀለት ሲሆን ነው፡፡

፪/ ደኑን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል በኮንሴሽኑ የሚሳተፉ ተጫራቾችን በግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ ይጋብዛል፣

፫/ የደን ኮንሴሽን አመልካች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ደኑን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል በተዘጋጀ ቅጽ የተሞላ ማመልከቻ፣

ለ) የድርጅት ምዝገባ ሰርተፍኬት ወይም የታደሰ የደን ንግድ ፍቃድ፣

ሐ) የግብር ከፋይነት ማረጋገጫ፣

መ) የውል ግዴታዎች አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9/ The contract signed with the government shall be terminated if communities do not comply with the obligations in Sub-Article 1 to 8 of this article and the obligations contained in the contract, fully or partially.

**19. <u>Prerequisites for Forest Concession, Bidding and Decision-Making</u>**

1/ A forest shall be transferred to another party under a concession contract if:-

a) It is demarcated and designated as protected or production forest with comprehensive information;

b) It has a forest management plan;

c) It has environmental and social impact assessment document.

2/ The government body owning and managing the forest shall invite interested parties to bid for the concession through an open tender notice.

3/ Bidders for forest concession shall submit the following documents:

a) Completed application form prepared by the concerned government body;

b) The company's registration certificate or renewed forestry business license;

c) Taxpayer identification number certificate;

d) Guarantee bond for the performance of contractual obligations.

፬/ አመልካቾችን ማወዳደሪያ መስፈርት

የደን ኮንሴሽን ጨረታ ለመወዳደር ያመለከቱ ተጫራቾች የሚወደዳሩት

ሀ) በኮንሴሽን ጨረታ የወጣበትን ደን ለማስተዳደር ባቀረበው ምክረ ሀሳብ፣

ለ) በኮንሴሽን ጨረታ የወጣበትን ደን ለማስተዳደር ባቀረበው ዋጋ፣

ሐ) የአመልካቹ ፋይናንሻል አቅም፣

መ) የአመልካቹ የሰው ሃይል፣

ሠ) በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙርያ ያካበተው ልምድ፣

ረ) ሌሎች የሚመለከተው የደን መስሪያ ቤት በሚያወጣቸው መስፈርቶች ይሆናል፡፡

፭/ የደን ኮንሴሽን በሚሠጥባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች በውድድር ወቅት መስፈርቱን አሟልተው ሲገኙ በመመዘኛው መሥፈርት ከሚያገኙት ውጤት በተጨማሪ ፲ ነጥብ በልዩ መንገድ ይሰጣቸዋል፡፡

፮/ የኮንሴሽን ውል ስምምነት ይዘት

ሀ) የመንግስትና የኮንሴሽነሩ መብትና ግዴታዎች፣

ለ) የደኑን ክልል የሚያሳይ ካርታና የደኑ ስፋት፣

ሐ) የስምምነቱ ዘመን ቢያንስ የአምስት ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የሚታደስ፣

መ) የውል ስምምነቱ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፯/ የኮንሴሽኔሩ መብቶች

ሀ) ኮንሴሽነሩ የአካባቢ ማህበረሰብ ወይም የደን ህብረት ስራ ማህበር ከሆነ ደኑን በባለቤትነት ከሚያስተዳድረው የመንግስት አካል የሙያ፣ ስልጠና፣ የህግ እና አስተዳደራዊ ድጋፍ የማግኘት፣

4/ Criteria for screening bidders

Bidders for forest concession shall be screened based on:

a) The quality of the proposal for managing the forest put on auction for concession;

b) The financial offer for managing the forest put on auction for concession;

c) The financial capacity of the bidder;

d) Size and quality of the bidder's workforce;

e) Extensive experience in forest development, protection and utilization;

f) Other criteria issued by the concerned forest office.

5/ When a community, living in areas where a forest is to be auctioned for concession, meet the screening criteria bidders it will earn additional 10 points in addition to the rating it gets from the screening;

6/ Content of the Concession Agreement

a) The rights and obligations of the government and the concessionaire;

b) A map showing the boundary and size of the forest;

c) The duration of the contract shall be at least five years, which shall be renewed as necessary.

d) The conditions for terminating the contract.

7/ Rights of the Concessionaire

a) To receive technical advice, training, legal and administrative support from the relevant government body if the concessionaire is a local community or forest cooperative;

CamScanner

ለ) በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ እና በኮንሰሼን ውል መሠረት ደኑን ማልማት፣ መጠበቅና መጠቀም

ሐ) ኮንሴሽነሩ የሚያስተዳድረው ደን ለሌላ የተሻለ ሀገራዊ እና ክልላዊ ጥቅም ለሚያስገኝ አማራጭ የሚውል ከሆነ አስፈላጊውን ካሳ የማግኘት፣ ዝርዝሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤

መ). ከካርበን ሽያጭ ከሚገኘው ጥቅም ፹ ከመቶ የመጠቀም መብት አለው፡፡

፰/ የኮንሴሽኔሩ ግዴታዎች

ሀ) በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኮንሴሽን ክፍያ የመፈጸም፣

ለ) ደኑን ከተረከበ በኋላ በውሉ የተጠቀሰውን ዋስትና በውሉ መሰረት ማስያዝ፣

ሐ) በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ እና የውል ስምምነት መሠረት ተለይተው የተቀመጡትን ተግባራት ማከናወንና በጽሁፍ ሪፖርት ማድረግ፣

መ) ከኮንሴሽኔሩ አቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ለሚመለከተው የመንግስት አካል በወቅቱ በጽሁፍ ሪፖርት የማድረግ፣

ሠ) በመንግስት በኩል ፈቃድ ያላቸው አካላት ለሚያካሂዷቸው የምርምር፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች የመተባበር፣

ረ) ከካርበን ሽያጭ ከሚገኘው ጥቅም ለፌደራል መንግሰት ፭ ከመቶ እና ለክልል መንግሰት ፲፭ ከመቶ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

b) To develop, protect, and utilize the forest according to the forest management plan and the concession contract;

c) To receive appropriate compensation if a forest managed under concession is to be converted to an alternate land use, which will provide greater national and regional benefits; details shall be determined by a Directive;

d) To use 80 percent of the income from the sale of carbon.

8/ Obligations of the Concessionaire

a) Shall pay for the concession within the time limit specified in the contract;

b) Deposit the guarantee indicated in the contract after the forest is handed over to him;

c) Implement the activities specifically outlined in the forest management plan and the contract, and submit a written report;

d) Timely report to the concerned government authority when encountered with a problem beyond the concessionaire's capacity;

e) Cooperate with authorized government body or individuals or organizations granted a permit by the government to conduct research, monitoring, and evaluation;

f) Pay 5 percent to the federal government and 15 percent to the regional government from the revenue gained from the sale of carbon.

፱/ በኮንሴሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖችን ለማልማት፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም የተሰጠ ውል የሚቋረጠው

ሀ) በዚህ ደንብና በኮንሴሽን ውል ውስጥ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ጥሶ ሲገኝ፣

ለ) የኮንሴሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖች ለሌላ የተሻለ ሀገራዊ እና ክልላዊ ጥቅም የሚያስገኝ አማራጭ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) ከተፈቀደው የኮንሴሽን ቦታ ውጭ ያለፍቃድ የደን ውጤቶችን መሰብሰቡ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

## ፳. የደን አያያዝ ዕቅድ

የደን አያያዝ ዕቅድ አዘገጃጀትና ማስጸደቅ ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩/ ለሰፋፊ ደን አልሚዎች የደን አያያዝ ዕቅድ የሚዘጋጀው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ባላቸው ባለሙያዎች ብቻ ይሆናል፣

፪/ በተፈቀደለት አካል የደን አያያዝ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት በደን ሀብት ላይ የመጠቀም መብት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ማማከር ይኖርበታል፣

፫/ በየደረጃው ደን ለማስተዳደር ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው አካል በደን አልሚዎች ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የደን አያያዝ ዕቅድ በመገምገም የማጽደቅ፣ እንደገና እንዲከለስ ወይም ውድቅ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

9/ A concession contract signed for the development, protection and utilization of forests shall be terminated:

a) If the concessionaire fails to comply with the provisions of this regulation and the concession contract;

b) When forests managed under a concession contract are found to be alternates for greater national and regional benefits;

c) When it is confirmed that forest products have been harvested outside the authorized concession area without a permit.

## 20. Forest management plan

The process for the preparation and approval of a forest management plan will be as follows:

1/ Forest management plan for large-scale forest developers shall be only prepared by professionals having a certificate of professional competence;

2/ When an authorized body prepares a forest management plan, he shall consult with stakeholders who have the right to benefit from the forest;

3/ The body authorized to manage forests at various levels shall be responsible for approving, requesting for revision or rejecting the forest management plan prepared and submitted by forest developers;

CamScanner

፬/ በደን አየያዝ ዕቅድ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ የሚያስከትል ሁኔታ ሲፈጠር የደኑ ባለቤት የደን አየያዝ እቅዱን በመከለስ ማስጸደቅ ይኖርበታል፣

፭/ የደን አየያዝ ዕቅድ የአድሜ ዘመን ሲያበቃ ደን አልሚው ደን ልማቱን ለማስቀጠል ከፈለገ አዲስ የደን አየያዝ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል።

4/ When a situation dictates that significant change shall be made in the forest management plan, the owner of the forest must revise the forest management plan and submit it for approval.

5/ When the lifespan of a forest management plan expires, the forest developer shall prepare a new management plan if he is interested in continuing with the development of the forest.

## ክፍል ሰባት
## የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### ፳፩.የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

፩/ ሀገራዊ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን በተገቢው መንገድ ለመምራት ከሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መ/ቤቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

፪/ የማህበረሰብ ደን አልሚ ህጋዊ ዕውቅና እንዲኖረው የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ ለመጥፋት የተቃረቡ ሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች እንዲጠበቁ በጥናት ተለይተው ሲቀርቡለት መርምሮ ያጸድቃል፣ እንደየተጋላጭነታቸው ደረጃ የዝርያዎችን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል፣

፬/ እንደአስፈላጊነቱ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የደን ውጤቶችን በዓይነትና በመጠን እንዳይገቡ ወይም እንዳይላኩ ሊፈቅድ ወይም ሊያግድ ይችላል፣

## PART SEVEN
## DUTIESAND RESPONSIBILITIES OF EXECUTIVE BODIES

### 21.Duties and Responsibilities of The Ministry

1/ Put in place a robust operational system for leading national forest development, protection and utilization efforts in collaboration with concerned federal and regional institutions;

2/ Issue Directives for providing legal recognition to community forest developers;

3/ Approve the protection of endangered indigenous tree species based on scientific study, and issue Directives for the development, protection and utilization of the species according to their level of vulnerability.

4/ Permit or prohibit the import or export of forest products' type and quantity as appropriate;

CamScanner

፭/ የደን ሙያ፣ የደን ልማትና የደን ውጤቶች ንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፤

5/ Prepare operational guidelines for issuing certificate for competence in forestry, forest development, and trading in forest products;

፮/ የደን በሽታና የደን እሳት አደጋ ከክልሎች አቅም በላይ ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው ከብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ጋር በመተባበር ሀገራዊ አቅምን በማቀናጀት የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ይሰራል፤ ሀገራዊ አደጋው ከሀገር አቅም በላይ ከሆነ አለም አቀፍ ድጋፍ ይጠይቃል፡፡

6/ The Ministry shall collaborate with the National Disaster Management Commission to coordinate national capacity for preventing and controlling the disaster when it receives information concerning incidences of forest disease and fire outbreaks that are beyond the capacity of regions; it shall call for international support if the disaster is found to be beyond the country's capacity.

## ፳፪. የኢትዮጵያ ደን ልማት

የኢትዮጵያ ደን ልማት ተግባርና ኃላፊነት፡-

፩/ ሀገራዊ የደን መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃ መዝግቦ ይይዛል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚዎችም ተደራሽ ያደርጋል፣

፪/ የሀገሪቱን የደን ሀብት ቆጠራና የሥርዓተ-ምህዳር ግልጋሎት አቅርቦቶችን ክትትል በየአምስት ዓመቱ ያካሂዳል፣ በቆጠራ የተገኘውን መረጃ ተንትኖ ለግምገማና ለቀጣይ ዕቅድ ዝግጅት በሚውል መልኩ ያደራጃል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም መረጃውን ያሳውቃል፣ .

፫/ ከፍተኛ ስርዓተ-ምህዳር አገልግሎት የሚሰጡ ደንና የደን መሬቶችን በጥናት ይለያል፤ የአገልግሎት ክፍያ ሥርዓት እንዲዘረጋ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

፬/ ከሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማት ጋር በመተባበር ለተለያዩ የደን ውጤቶች የንግድ መደብ መስፈሪያ ኮድ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

## 22. Ethiopian Forestry Development

The Ethiopian Forestry Development shall have the following duties and responsibilities:-

1/ Organize a national forest database, document, and stores information, analyze, and make it accessible to users.

2/ Conduct forest inventory and monitor the provision of ecosystem services every five years; analyze the data gathered through the inventory and organize it for evaluation and planning and share the information with concerned parties;

3/ Identify forests and forest lands that provide significant ecosystem services; submit a proposal to the Ministry to establish a system for payment for ecosystem services;

4/ Establish trade code for different forest products in collaboration with the relevant federal institutions.

CS CamScanner

፭/ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የልማት አጋር አካላት ያላቸውን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችል የጋራ መድረክ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፤

፮/ የውጭ ባለሀብቶች በሀገር ውስጥ ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዘርፍ እንዲሳተፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፯/ በመጥፋት ላይ ያሉ የዛፍ ዝርያዎችን በጥናት በመለየት ዝርዝር መረጃ ይይዛል፣ ጥናቱን መሰረት በማድረግ እንደየ ተገላጭነታቸው ደረጃ የዛፎችን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ያስወስናል፣ ውሳኔውን ከክልሎች ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆን ይሰራል፣

፰/ የደን በሽታና የደን እሳት አደጋን መተንበይ፣ መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እና ሀገራዊ አቅም ይገነባል፣ አደጋዎችን የመተንበይ፣ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎችን ከክልሎች ጋር በመተባበር ይሰራል፣

፱/ ደን ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ከክልሎች አቅም በላይ ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው ለሚኒስትሩ ወዲያውኑ ሪፖርት ያቀርባል፣

፲/ የደን ትምህርት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ የስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት ይሰራል፣

5/ Establish a stakeholder forum to strengthen the participation of government institutions, non-governmental organizations and development partners involved in forest development, protection, and utilization.

6/ Facilitate the engagement of foreign investors in forest development, protection, and utilization in collaboration with relevant parties;

7/ Document the list of threatened tree species identified through research, prepare draft guidelines based on the research findings for the development, protection and utilization of the trees according to their level of vulnerability, and submit it to the ministry for decision; work in collaboration with regions to implement the decision;

8/ Build a system and national capacity for early warning, preventing and controlling forest diseases and forest fires; work in collaboration with regions to provide early warning information, prevent and control disasters;

9/ Report immediately to the Ministry upon receiving information about the occurrence of forest disasters beyond the response capacity of the regions;

10/ Ensure forestry is included in the curriculum of regular education starting from primary schools;

CS CamScanner

፲፩/ በከፍተኛ የትምህርትና የሙያ ተቋማት የሚሰጡ የቀለምና የሙያ ትምህርቶች የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን ለማዘመን የሚያስችል ሥርዓተ-ትምህርት እንዲኖራቸው ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፪/ የደን አያያዝ ዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት እና የዕቅዱ ይዘት እንዲሁም የሚጸድቅበት ሂደት የሚገልጽ የቴክኒክ ማኑዋል ያዘጋጃል፤

፲፫/ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር አሰራሮችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፳፫.<u>የክልልና የከተማ አስተዳደሮች ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩/ ከሚመለከተዉ ተቋም ጋር በመሆን በክልሉ የሚገኙ የምርት ሰጪ፣ ጥብቅ ደኖችን እና ፍጹም ጥብቅ በዚህ ደንብ በወጣው መመዘኛ መሠረት ይለያል፣ ይሰይማል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ አሁን ያለው አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ በቀጣይ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሲዘጋጅ በሚወጣው በዕቅዱ መሠረት የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫/ በአሳታፊ የደን አያያዝ ወይም በኮንሴሽን ውል የሚተዳደሩ ደኖችን ይለያል፤ በዚህ ደንብ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፣

፬/ በኮንሴሽን ውል ለሚተዳደሩ የመንግስት ደኖችን በተመለከተ፣

11/ Support higher education and vocational training centers that provide theoretical and practical trainings with a curriculum that can modernize forestry development, protection and utilization activities;

12/ Develop a technical manual describing the process for developing a forest management plan, its contents and the procedure for approval;

13/ Prepare detailed procedures to ensure the implementation of this regulation.

23. <u>Duties and Responsibilities of Regional States and City Administrations</u>

1/ In collaboration with the relevant institutions, identify, designate and manage production, protected and reserve forests based on the criteria specified in this regulation;

2/ Notwithstanding the current practice, implement forest development, protection and utilization activities according to the land use plan that shall be issued;

3/ Identify forests that can be managed through participatory forest management or under concession scheme and manage the forest in accordance with this regulation;

4/ Regarding forests managed under concession contract;

CamScanner

ሀ) በደኑ ውስጥ የሚመረተውን የደን ውጤት ዓይነትና መጠን የኮንሰሽን እና የዋስትና ዋጋ ይተምናል፤ አፈጻጸሙን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

ለ) የኮንሰሽን ሰነድ ያዘጋጃል፤

ሐ) ኮንሴሽነሩ በውሉ የተጠቀሰውን ዋስትና ማስያዙን ያረጋግጣል፤

መ) በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ የኮንሴሽን ክፍያ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

ሠ) የተዘጋጀውን የደን አያያዝ ዕቅድ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ረ) ከሚያገኘው ገቢ ፲ ከመቶ ለአካባቢው ማህበረሰብ ልማት እንዲውል ያደርጋል፤

ሰ) በየደረጃው ያለው የደን መስሪያ ቤት ከኮንሴሽን የሚያገኘውን ገቢ በቀጥታ ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እንዲያውል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

ሸ) ውል ሲቋረጥ የመንግስት አካል ውል መሠረዙን ውሉ ለተሰረዘበት አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፤

ቀ) ለአካባቢው ህብረተሰብም በማስታወቂያ ሰሌዳ በመለጠፍ እንዲያውቁት ያደርጋል፤

በ). ከደን ባለቤትነት ጋር ተያይዞ ለሚነሱ የመብት ጥያቄዎች ለሶስተኛ ወገን ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፤

፭/ በክልል ያሉ የደን ሀብቶች ከደን እሳት አደጋ እንዲጠበቁ የደን እሳት መከላከል እና መቆጣጠር ሥርዓት በሁሉም የአስተዳደር እርከን ይዘረጋል፤

a) Assess and estimate the type and quantity of forest products produced in the forest, the monetary value of the concession and the guarantee bond, and develop an operational system for implementation;

b) Prepare a document for concession;

c) Ensure that the concessionaire has submitted the guarantee bond according to the agreement;

d) Ensure that the concession payment is made within the deadline specified in the contract;

e) Monitor the implementation of the forest management plan;

f) Shall pay 10 percent of the income for local community development;

g) Work with relevant parties to monitor the extent to which forest offices at various levels are using the revenue from the concession for the development, protection and utilization of forests;

h) Notify, in writing, the concerned party that the agreement has been terminated by the relevant government body;

I) Inform the local community about the termination of the agreement by posting a notice on a public display board;

j) Has a responsibility to respond to inquiries that may be raised by a third-party concerning forest ownership rights;

5/ Establish fire prevention and control system at all levels to protect regional forest resources from forest fire;

CamScanner

፮/ የእሳት አደጋ ከመከሰቱ በፊት ቅድመ ትንበያ መረጃ ይሰበስባል፣ ለተጠቃሚዎች የጥንቃቄ መልዕክት ያሰራጫል፣ አደጋው ሲከሰት ከክልሉ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ጋር በመተባበር የመከላከል ስራ ይሰራል፣ የመከላከሉ ስራ ከክልሉ አቅም በላይ ሲሆን ለኢትዮጵያ ደን ልማት በፍጥነት ያሳውቃል፣

6/ Gather early warning information before the incidence of fire; disseminate report for warning users; collaborate with the Regional Disaster Management Commission to take preventive measures when disaster occurs; inform the Ethiopian Forest Development when the capacity to prevent the disaster is beyond the response capability of the region;

፯/ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፓኬጆችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

7/ Develop and implement information and technology packages forest development, protection and utilization;

፰/ የደን አጠቃቀሙ ከአካባቢው የደን ሀብት አቅም በላይ እንዳይሆን የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

8/ Closely monitor and control the utilization of forest resources does not exceed the allowable harvest;

፱/ ደንና የደን መሬቶች ከሚመለከተው አካል የይዞታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲያገኙ ያደርጋል፣

9/ Ensure that forests and forest lands shall be issued with certificate of land holding from the concerned government authority;

፲/ የይዞታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መሠረት በማድረግ የደን ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣል፣

10/ Issue forest ownership certificate based on land holding certificates;

፲፩/ ክልላዊ የደን መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃ መዝግቦ ይይዛል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚዎችም ተደራሽ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው የፌደራል እና ሌሎች ተቋማት መረጃ ያስተላልፋል፣

11/ Organize forest database at regional level, document, store and analyze data, provide access to users, and share information with concerned federal and other institutions;

፲፪/ በክልል ደረጃ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ የሚከናወኑ ስራዎችን በየሩብ አመቱ ለኢትዮጵያ ደን ልማት ሪፖርት ያደርጋል፣

12/ Submit quarterly report to the Ethiopian Forestry Development on forest development, protection and utilization activities undertaken at regional level;

፲፫/ በህገወጥ መንገድ የተያዙ የደን መሬቶችን በማስመለስ መልሰው ለደን ልማት እንዲውሉ ያደርጋል፣

13/ Repossess illegally appropriated forest lands and use them for forest development;

፲፬/ ኬላዎችን በአስፈላጊ ቦታዎች በማቋቋም የደን ምርት ዝውውር ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ያደርጋል፣

14/ Control and monitor the transportation of forest products by establishing checkpoints at appropriate locations;

፲፭/ ለደን አልሚዎች የተፈቀደውን መብቶችና ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ግዴታዎችንም ያስፈጽማል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፬.የከተማ ደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀምና አስተዳደር

፩/ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች በራሳቸው ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ከግል ባለሃብቶች ጋር በመተባበር በተገቢው ቦታ የከተማ ደንን ያለማሉ፣

፪/ በየደረጃው ያሉ የደን ልማት መስሪያ ቤቶች ለከተማ ደን ልማ፡ ምስረታ፣ አያያዝና አጠቃቀም ተገቢውን የደን አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣ ሌሎች አስፈላጊ የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይተባበራሉ፣

፫/ የከተማ ደን ባለቤቶች በተዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት የከተማ ደን ልማቱን ያስተዳድራሉ፡፡

### ፳፭.ለአካባቢ ጥበቃ ዓላማ የለማ ደን ጥበቃና አጠቃቀም

፩/ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና አስተዳደር ጋር በመመካከር ለአካባቢ ጥበቃ ዓላማ የሚውሉ ዝርያዎችና የሚለመቡት ቦታዎች መለዬት፣

፪/ አላማቸውን እና አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ከአካባቢው ማህበረሰብ ወይም ተቋማት ጋር በመመካከር የደን አያያዝ ዕቅድ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

15/ Be compliant in implementing the rights and incentives granted to forest developers; enforces the execution of obligations.

## PART EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 24. Urban Forest Development, Protection, Utilization and Management

1/ Regions and city administrations shall develop urban forest on appropriate sites on their own or in collaboration with non-governmental organizations or private investors;

2/ Forest development offices at various levels shall develop appropriate forest management plan for the establishment, management and utilization of urban forest; they shall also collaborate regions and city administrations in providing technical advice as appropriate;

3/ Urban forest owners shall manage the urban forests in accordance with the forest management plan.

### 25.Conservation and Use of Forest Developed for Environmental Protection

1/ In consultation with the local community and administration, identify species and sites for environmental protection;

2/ Consult with local communities and institutions concerning the purpose of forests to be developed for environmental protection and prepare a management plan.

CamScanner

፫/ ሥርዓተ-ምህዳሩ ወይም ተፋሰሱ ከጎርፍ፣ ከደለል፣ ከመሬት መንሸራተት እና ከሌሎች መሰል አደጋዎች ለመከላከል በህብረተሰቡ ተሳትፎ ከሰውና ከእንስሳ ንኪኪ ተጠብቀውና የደን አያያዝ ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው በዘላቂነት ይለማሉ፣ ጥቅም ላይም ይውላሉ፡፡

3/ Ecosystems or watersheds shall be protected from floods, sedimentation, landslide, and other disasters; human and animal interference shall be prevented through the participation communities and a forest management plan shall be developed for their sustainable development and utilization.

**፳፮. <u>የደን አደጋዎችን መከላከል</u>**

ማንኛውም አካል በደን ውስጥ መሰረተ ልማቶችን ከመዘርጋቱ፣ ማዕድን ከማምረቱ ወይም ሌሎች ኢንቨስትመንቶችን ከማካሄዱ በፊት ደኑን ከሚያስተዳድረው የክልል ወይም የፌዴራል አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

**26. <u>Prevention of Forest Disasters</u>**

Without prejudice to the Proclamation, any party must have permission from the regional or federal government responsible institution for managing the forest before developing infrastructure, producing minerals, or undertaking other investment activities in the forest.

**፳፯. <u>የደን ውጤቶችን ማምረትና ማዘዋወር የደን ውጤቱ</u>**

ከቦታ ቦታ በሚዘዋወርበት ጊዜ የክልል አስፈጻሚ አካል ከሚሰበስበው የሮያሊቲ ገቢ የተወሰነውን ድርሻ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ለደን ልማት ማዋል ይኖርበታል፡፡

**27. <u>Production and Distribution of Forest Products</u>**

Without prejudice to the Proclamation, a regional executive body shall allocate a portion of the revenue from royalty fee for forest development.

**፳፰. <u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>**

፩/ በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኝ ደን ወይም የደን መሬት በግል ይዞታ ማስመዝገብ ወይም መጠቀም፣

፪/ በደን አያያዝ ዕቀዱ መሠረት ከተፈቀደለት መጠን በላይ የደን ምርት ማምረት፣

**28. <u>Prohibited Activities</u>**

Without prejudice to the prohibitions in the Proclamation:

1/ Registering or using forest or forest land under government holding as private holding;

2/ Producing forest products in excess of the quantity allowed based on the forest management plan;

CamScanner

**፳፱. ቅጣት**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ የተላለፈና የመንግስትን ደን በግል ይዞታ አስመዝገብ ወይም ጥቅም ላይ አውሎ ከተገኘ በግል የተመዘገበው ደን ለመንግስት ይዞታነት ማስመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፣

፪/ በደን አያያዝ ዕቅዱ መሠረት ከተፈቀደለት መጠን በላይ የደን ምርት ያመረተ ከተፈቀደለት በላይ ያመረተውን ምርት መጠን በሚያለማው ደን ላይ እስከሚያካክስ ድረስ የማምረት ፈቃድ ይከለከላል፣

**29. Penalty**

1/ If the provisions of Sub-Article 1 of Article 28 of this Regulation have been passed and the state forest has been registered or found to be in private possession, the privately registered forest will be subject to the return to the state land holding; the person who registered the state forest as a private possession will be held liable under the appropriate criminal law,

2/ Any person who produces more than the allowed amount of forest products in the first harvest season based on the forest management plan will be denied a second round of production license until he compensates the amount of products that he produced more than the allowed amount in the first harvest period.

**፴. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**30. Inapplicable laws**

No Regulation or Directive or customary practices that contradict this regulation shall be applicable to matters stipulated in this regulation.

**፴፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**31. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

**Done at Addis Ababa, on this 4th Day of April, 2024**

ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

CamScanner